# የስትሮክ ምልክቶችን ያውቃሉ?

| F | A | S | T |
|---|---|---|---|
| Face | Arm | Speech | Time to hospital |
| ፊት | እጅ | አነጋገር | ሰአት |

**<u>የፊት አንድ ጎን መደንዘዝ</u>**

ፈገግ ለማለት ሲሞክሩ ፈገግ ማለት አለመቻል ወይም አንድ የከንፈር ጫፍ ወደላይ ሌላኛው ወደታች መቀልበስ

**<u>የአንድ እጅ መዛል</u>**

ሁለቱንም እጅ ከፍ ለማድረስ ሲሞክሩ አንድ እጅ አልታዘዝ ማለት። ሁለቱንም እጅ ከፍ ማድረግ ይችላሉ፤ ነገር ግን አንድ እጅ ዝሎ ወደታች ይወርዳል።

**<u>የአነጋገር መጎተት</u>**

መናገር ይከብዳል
የሚናገሩት ነገር ትርጉም አይሰጥም
ቀላል አርፍተ ነገር ደግመው እንዲናገሩ ሲጠየቁ ለመድገም ይቸገራሉ።

**<u>በተቻለ ፍጥነት ሆስፒታል መሄድ</u>**

እነዚህ ለውጦች በድንገት ሲታዩ ቶሎ ወደሆስፒታል መሄድ ያስፈልጋል።

**<u>ከነዚህ ውጭ ሌሎች የስትሮክ ምልክቶች</u>**

- ድንገት የሰውነት መደንዘዝ ወይም በግማሽ የሰውነት ክፍል ሰውነትን ማዘዝ አለመቻል።
- ድንገተኛ የማገናዘብ ችሎታ መቀነስ፣ ለመናገር መቸገር ወይም ሌላ ሰው የሚናገረውን መረዳት አለመቻል
- ድንገት የማየት ችሎታን ማጣት
- ድንገት መራመድ አለመቻል ወይም የሰውነትን ሚዛን መጠበቅ አለመቻል።
- ድንገተኛ፣ ምንም ምክንያት የሌለው ሀይለኛ ራስምታት

## ህክምና ለማግኘት የሚፈጀው እያንዳንዱ ደቂቃ ለውጥ ያመጣል

በአንጎል ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ እና ህክምና ለማግኘት ምልክት ከታየ በሶስት ሰአት ውስጥ ሆስፒታል መድረስ ያስፈልጋል።

Adapted from American Heart Association at https://www.stroke.org/en/about-stroke/stroke-symptoms(Aug 4, 2019)